# መብቶችዎን ይወቁ

VOTE 2025

### እንደ ኣንድ የሚኖሶታ ድምጽ ሰጪ ኣያሌ መብቶች ኣሎት- እወቁዋቸው!

## ለመምረጥ ከስራ የእረፍት ጊዜ ይውሰዱ

በቀሪ የድምጽ መስጫ ጊዜ ወይም በምርጫ ቀን ክፍያዎን፣ የግል እረፍትዎን ወይም የመዝናኛ ጊዜዎን ሳያጡ ድምጽ ለመስጠት ከስራ እረፍት የመውጣት መብት አለዎት።

## (እንደ ኢትዮጵያ ኣቆጣጠር) እስከ ምሽቱ 2 ሰዓት ድረስ ሰልፍ ላይ ከሆኑ መምረጥ ይችላሉ።

እንደ ኢትዮጵያ ኣቆጣጠር ከምሽቱ 2 ሰዓት ድረስ ሰልፍ ላይ ከሆኑ (በፈረንጆች ኣቆጣጠር 8 P.M) የመምረጥ መብትዎ የተጠበቀ ነው።

## በምርጫው ዕለት መመዝገብ

የት እንደሚኖሩ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከያዙ፡ በምርጫው ዕለት ተመዝግበው የመምረጥ መብት ኣሎት።

## በቃልዎ መፈረም

ራስዎ ፊርማዎን መፈረም ካልቻሉ፡ ማን መሆንዎን በቃልዎ ኣረጋግጠው ሌላ ሰው እንዲፈርምልዎ የማድረግ መብት ኣሎት።

### የ2025 ቀናት

የማጣርያ ምርጫ
ማክሰኞ፡ ነሃሴ 12 ቀን

በኣካል ሳይገኙ የሚደረግ ምርጫ
በፖስታ መምረጥ ወይም በኣካል ተገኝተው የሚመረጥበት ቀን - ከመስከረም 19ቀን እስከ ህዳር 3 ቀን

ለመምረጥ ተመዝገቡ
በዋናው ምርጫ ቀን፡ ግዜ ለመቆጠብ ቀደም ብለው በግዜ እስከ ጥቅምት 14 ቀን ለመምረጥ ይመዝገቡ።

የምርጫ ቀን
ማክሰኞ ህዳር 4 ቀን

## እርዳታ መጠየቅ

ከአሰሪዎ ተወካይ ወይም ከማህበሮ ወኪል በስተቀረ፤ ከሌላ ከማንኛውም ሰው እርዳታ መጠየቅ ይችላሉ።

## ወደ ምርጫው ጣብያ ልጆችን ማምጣት

ልጆችዎን ከእርስዎ ጋር ወደ ምርጫው ጣብያ ማምጣት መብትዎ ነው።

ከበስተጀርባ ይቀጥላል...

# መብቶችዎን ይወቁ

VOTE 2025

...ከበፊቱ ገጽ የቀጠለ

## በአሁኑ ጊዜ በከባድ ወንጀል ተይዘው ካልታሰሩ ድምጽ ይስጡ

በከባድ ወንጀል የተከሰሱ ከሆነ፣ በአሁኑ ጊዜ በከባድ ወንጀሉ የታሰሩ ካልሆኑ ድምጽ መስጠት ይችላሉ።

## በሰው ጥበቃ ስር እያሉ መምረጥ

በሰው ጥበቃ ስር እያሉም፡ የመምረጥ መብትዎ በዳኛ እስካልታገደ ድረስ፡ የመምረጥ መብት ኣሎት።

## በሌላ ሰው የማሳመን ተጽእኖ ሳይደረግቦ መምረጥ

በምርጫው ጣብያ ውስጥ ማንም ሰው ምርጫዎን ለማስቀየር ጫና ሳያደርግቦ የመምረጥ መብት ኣሎት።

## ሌላ ቅያር የምርጫ ወረቀት ማግኘት

የምርጫ ሳጥን ውስጥ የመረጡትን ሰው ስም ከማስገባትዎ በፊት ተሳስቸለሁና ሌላ ኣዲስ ቅያር የምርጫ ወረቀት ስጡኝ የማለትና የማግኘት መብት ኣሎት

## ቅሬታ መግለጽ

የምርጫውን ኣካሄድ በሚመለከት ኣንዳች ቅሬታ ቢኖሮት፡ በኣከባቢዎ ላለው ኣስመራጭ ኮሚቴ ቅሬታዎን በጽሁፍ የማስመዝገብ መብት ኣሎት።

## ለዓይነት የሚሆንዎ የምርጫ ወረቀት ወደ ምርጫው ቦታ ማምጣት

ለዓይነት የሚሆንዎ የምርጫ ወረቀት ወደ ምርጫው ቦታ የማምጣት መብት ኣሎት።

## የመራጮችን መብቶች ያለበትን ህጋዊ ወረቀት ማምጣት

የመራጮች መብቶች በዝርዝር ያለበትን ህጋዊ ወረቀት ወደ ምርጫው ቦታ የማምጣት መብት ኣሎት።

የሚኖሶታ የኣገር ውስጥ ኣስተዳደር ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት

mnvotes.gov • 1-877-600-VOTE